# ኑሮ በሀዘን
(ከቤተሰቦቹ)

ዝክር ለሣሙኤል ለዘላለም
ሸማህ የፍትህ ነው ካባህ የሰላም።
ሌቱ ለቀን ቢለቅ ክረምትም ለበጋ
ሕዝብ አክብሮትህ ምክርህ ከእኛ ጋ።
በአካል ባትኖር መንፈስህ ግን አለ
ልባችንም ከስሎ ሣሙኤል እያለ
ሀዘን አኮራምቶን ቅስማችን ተሰብሮ
አለንልህ ሣሚ ከተባለ ኑሮ።
እየከበደ እንጂ ሲቀል አላየነው
አለመመለስከን መች ነው የምንለምደው?
ሁለት ዓመት ጊዜ ሁለት መቶ ይመስላል
ካንተ ተለይቶ መቀጠል ከብዶናል።
ጉጉትህ ለሠላም ለሀገር ፍቅርህ
ትኩስ ነው ሣምዬ ያንተ ትዝታህ።
የአላማ ፅናትክን ለማን አወረስከው
የጀመርካቸውን ማን ሊያጠናቅቅ ነው?
በሞት ድል ተነስተህ ጨክነህ የቀረኸው።
አልተቀበልን እኛ አላመንም ከቶ
ጉድጓድ መግባትህን ልባችን ዘንግቶ።
ሳቅህ ይሰማናል በተደጋጋሚ
ሁሌም ከእኛ ጋር ነህ አትዘንጋ ሣሚ።
የፍኖት የፍቅር የፅናቱ መሪ
ለሚያውቅህ ሁሉ ለወገንም አኩሪ።
ትክክል ሚዛኑን የማታጓድል
አንተን ማጣት ከቶ አለመታደል።
ናፈቅከን ሣሙኤል ራቀ ድምፅህ
የፍትህ ርትዕ የአንድነት ድምፅህ።
መቼ ለት ሰመረ መች ተጠቃለለ
አንተን ይዞብን ሞት የኮበለለ?
ሻማና ጧፉ ይብራ ለዓላማህ
ለህዝብም አርነት ይስመር ፍታትህ።
ስራህም ድካምህ ለድሀው ሰው ብቻ
ታላቅ ሰው የነበርክ ያላገኘህ አቻ።
የማይረሳ ነው በሳ ዓላማህ
ሁሌም የሚናፈቅ ያ አሳሳቅህ።
አልተወገደ ከፊታችን
ደምቆ ይቀመጣል ከልባችን
ይዘዋወራል በደም ስራችን።

በጣም ይመራል የሀዘን ኑሮ
እየተፋጀ ጠዋት ማታ እሮሮ።

ዝም አለ ሣሙኤል ሄደብን በቃ
ቃሉን አክብሮ ምኔም ሳይነቃ።
ቀረብን ለእኛ አሳደለን
ያለውን ከእኛ ያቀፍነውን
እናወራለን ነበር ብለን።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com